# መልስ ለአቶ ብርሃነመስቀል የ"ኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች" ባሉት ላይ

ግርማ ካሳ

Monday, February 8th, 2016

አቶ ብርሃኑ መስቀል አበበ፣ በኦሮሞ ብሄረሰብ ሙብት ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ጽሁፎችን ይጽፋሉ። ቢቢሲ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ስርጭት እንዲኖረው ፔቲሽኖችን በማስፍረም አንድ ዘመቻ እንደነበረ የምናስታወሰው ነው። ይሄንን ዘመቻ ይመሩ ከነበሩት መካከል አቶ ብርሃነመስቀል አንዱ ነበሩ። እኔም ሆንኩም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፔቲሽኑ ላይ ፊርማችንን በማስፈር ፣ ፔቲሽኑ ያልፈረሙ እንዲፈረሙ በማበረታታት እንደነ አቶ ብርሃነ መስቀል ባይሆንም፣ የድርሻችንን አበርክተናል። ላለፉት ሶስት ወራት በኦሮሚያ በተነሳው ተቃዉሞ ዙሪያ፣ አቶ ብርሃነመስቀል "የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው" ያሉትን ስድስት ጥያቄዎች አስቀምጠዋል።

"የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ለልመናም ሆነ ለድርድር የሚቀርቡ አይደሉም። ጀግናው እና ደጉ የኦሮሞ ሕዝብም የልመና ባህልም ሆነ የለማኝ ተወካይ የለውም፣ ኖሮትም አያውቅም። ሙብቱንም ያስከብራከል እንጂ አይለምንም።" ሲሉ በጥያቄዎቹ ዙሪያ ድርድር እንደሌለ በአድን በኩል ይጽፉና ወረድ ብለው ፣ አቶ ብርሃነመስቀል ድርድር እንደሚያስፈለግ ይገልጻሉ። እርስ በርስ የሚቃረኑ አባባሎች።

አንደኛ "የልመና ባህል የለዉም፣ አይለምንም …" የሚሉት አይነነት አባባሎች መንፈሳቸው ጤናማ አይደለም። አቶ ብርሃንመስቀል ይሄን አይነት፣ "እኛ ያልነው ካልሆነ " የሚመስል አባባል በመጠቀም ሌላውን ለማስፈራራት መሞከሩ ጠቃሚ አይመስለኝም። ሁለተኛ አቶ ብርሃነመቀል የኦሮሞ መሬት የሚሉት የኦሮሞዎች ብቻ እንዳልሆነ የዘነጉትም ይመስላል። የኦሮሞ መሬት የሚሉት የሁሉም ኢትዮጵይያዊ ነው። ሌላውም መሬት የኦሮሞዎች እንደሆነው። ሶስተኛ የኦሮሞ ሕዝብ አይለምንም እንዳሉትም፣ የሶማሌ ሕዝብ፣ የጉራጌ ሕዝብ፣ የሲዳማ ሕዝብ፣ የአዲስ አበባ ህዝብ ..ሌላውም አይለምንም።

"የኦሮሞ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ ጋር በጋራ የመኖር ጠቀሜታና አስፈላጊነትን በሚገባ ስለሚገነዘብ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ በተመሠረተ የሰጥቶ መቀበል የድርድር ሕግ ያምናል" ያሉት አባባል ግሩም አባባል ነው። እዚያ ላይ በማተኮር ላሉ ችግሮች ፣ ሁሉም አሸናፊ የሆነበት መፍትሄ መፈለጉ ላይ የበለጠ ቢሰሩበት ጥሩ ይሆናል ብዬ አማናለው። አቶ ብርሃኑ መስቀል ባቀረቧቸው ሐሳቦ ላይ ግን መቀበል እንጅ መስጠትን አላየሁበትም። በአንድ ወግን ያለውን ፍላጎት ብቻ ያንጸባረቀ እንጅ በሌላው ወግን የሚነሱትን ጥያቄዎች ከግምት ያስገባ አይመስለኝም። እንግዲህ ሰጥቶ የመቀበል መርህ ማለት መቀብል እንዳለበትም ሁሉ መስጠት አለበት።

አቶ ብርሃነመስቀል የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው ብለው ሲጽፉ፣ አንደኛ በምን መስፈርትና ሚዛን እነዚህ ጥያቄዎች የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄውም ስለሞሆናቸው የገለጹልን ነገር የለም። እንዴት አወቁ የኦሮሞ ሕዝብ ያሉት ጥያቄዎቹ እነዚህ እንደሆኑ ? ሁለተኛ የኦሮሞ ሕዝብ የሚሉት የትኛውን ሕዝብ ማለት እንደሆነ የጠራ መመዘኛ ያቀረቡ አይመስለኝም።፡የኦሮሞ ሕዝብ የሚባልው በኦሮሚያ የሚኖረው ወይንም የክልሉ ነዋሪዎች ማለቱ ነው ? ወይስ አፋን ኦሮሞ አንደኛ ቋንቋዉ የሆነው ማህበረሰብ ማለታችቸው ነው ? ወይስ ራሳቸዉን ኦሮሞ ነን ብለው የሚጠሩ ወገኖች ስብስብን ነው የኦሮሞ ሕዝብ የሚሉት ?
ይሄን ስል ግን ጥያቄዎቹ መነሳት የለባቸው ማለቴ አየደለም። ግን አቶ ብርሃነመስቀል የ"ኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው" ብለው ከሚያቀርቧቸው "ያሉ ችግሮችን ለመፍታት መመለስ አለባቸው የምላቸውም ወይንም የኦሮሞ ጥያቄዎች ናቸው ብዬ የማስባቸው ጥያቄዎች ናቸው" ብለው ቢያቀርቡት መልካም ይሆን ነበር። እኔም ጥያቄዎች እንደ ኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ሳይሆን በአቶ ብርሃነ መስቀል የተነሱ ጥያቄዎች አድርጌ ሐሳብ እሰጥባቸዋለሁ፡

1. "በጉልበት እና ሕግን ሽፋን በማድርግ የተዘረፈው የኦሮሞ ሕዝብ መሬት እንዲመለስ፣ የወረራው መሠረት የሆኑት ሕጎች እንዲሻሩና የዘረፉ ተቋማቶቹ እንዲፈርሱ፣" ይላሉ አቶ ብርሃኑ መስቀል።

ትክክል ብለዋል። ሆኖም የኦሮሞ ሕዝብ መሬት የሚለው አባባል አይመቸኝም። ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ ይህ አባባል የተወሰኑ ቦታዎች የኦሮሞ መሬት፣ ሌላው ደግሞ የሌሎች መሬት እንደሆነ የሚያመላክት አባባል ይመስለኛል። ሁሉም የኢትዮጵያ መሬት የኦሮሞዎች መሬት ነው። ሁሉም የትግሬዎች መሬት ነው። በመሆኑም በምትኩ "በጉልበትና ሕግን ሽፋን

በማድረግ ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችን መሬታቸው እንዲመለስ" የሚል አባባል ቢጠቀሙ ጥሩ ይሆን ነበር።

"የመሬት ነጠቃዉ መሰረት የሆኑ ሕጎች እንዲሻሩም'' ሲሉ ጽፈዋል። ይሄንን ሲጽፉ፣ በሕገ መንግስቱ የተቀመጠውን "መሬት መሸጥና መለወጥ አይቻልም፣ መሬት የመንግስት ነው'' የሚለውን አባባል ለምን እንዳልጠቀሱ አልገባኝም። አንዱና ትልቁ ችግር መሬት የአራሹ አለመሆኑ ነው። ገበሬው የመሬቱ ባለቤት መሆኑ በህግ እስካልተቀመጠ ድረስ ገበሬዉን እና ድሃ ከተሜዎች እንዳይፈናቀሉ ሊያስቆም የሚችል የሕግ መሰረት አይኖርም። ብዙ የኦሮሞ ብሄረተኞች ገበሬዉ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን አይፈለጉም። መሬቱ የመገርሳ፣ የቶላ፣ የቀልቤሳ፣ የቱሉ ..ከሆነ መሬቱ የነዋሪዎቹ እንጂ የኦሮሞ ብሄረሰብ መሆኑ ይቀራል። በኦሮሚያ ዉስጥም እነ ጎይቶም፣ እነ ሽምሹ፣ እነ አበጋዝ ፣ እነቤርሳሞም የመሬት ባለቤት ይሆናሉ። ያንን የኦሮሞ ብሄረተኞች አይፈልጉም። እንደ ኦፌኮ ያሉ ደርጅቶች በዚህ ምክንያት ነው መሬት ለአራሹን የማይደገፉት።

2. "ኦሮምኛ ከአማርኛ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ፌድራል መንግስት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን'' ሲሉ በሁለተኛነት አቶ ብርሃነመስቀል ያስቀምጣሉ።

ይሄም የሚደገፍ ሐሳብ ነው። አፋን ኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ሶማሌኛና ትግሪኛም ቢጨመሩ ጥቅም ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ። በተለይም ሶማሌኛ ተናጋሪ ከሆኑት ከሶማሊያ፣ ከሶማሌላንድና ጅቡቲ ጋር እንዲሁም ትግሪኛ ተናገሪ ከሆንችው ኤርትራ ጋር መቀራረቡን የበለጠ ለማጠናከር ይረዳል።

ቋንቋ በመሰረቱ ጠቃሚ ነገር ነው። ብዙ ቋንቋዎችን ማወቅ ጸጋ ነው። ብዙዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ቢችሉ ጥቅም አለው እንጂ ጉዳት የለዉም። ቋንቋ የመለያየት ምክንያት ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም። በቅንነት ነገሩን ካየነው ከአማርኛ ቀጥሎ ሌሎች ቋንቋዎችም ፌዴራል ቋንቋ መሆናቸው ተቃዉሞ ሊያስነሳ አይገባም።

ሆኖም በኦሮሚያ ክልል፣ ከአፋን ኦሮሞ ጎን አማርኛም የሥራ ቋንቋ የመሆኑ አስፈላጊነት ሊሰመርበት ይገባል። አቶ ብርሃነ መስቀል በዚህ ረገድ ጥቂት ቢሉ ጥሩ ነበር። በአዳማ ከ 75% በላይ የሚሆነው ነዋሪ አማርኛ ተናጋሪ ሆኖ ፣ የክልል መንግስት አገልግሎት በአማርኛ መነፈጉ፣ አፋን ኦሮሞ ባለመቻሉ የኦሮሚያ ክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጥሮ የመስራት፣ የመመረጥ መብቱ መረገጡ ተገቢ ነው ይላሉን ? አዳማን እንደ ምሳሌ ጠቀስኩ እንጂ በቡራዩ ከ 45% በላይ፣ በሻሸመኔ፣ ቢሾፍቱ ፣ ጂማ ባሉ ከተሞች ከ 60% አፋን ኦሮሞ የማይችሉ ኢትዮጵያውዉያን ይኖራሉ። አዲስ አበባን ጨመሮ በአራቱም የኦሮሚያ የሸዋ ዞኖች ከ 44% በላይ ሕዝብ አፋን ኦሮሞ አይናገረም። ታዱያ ይሄን ያህል እጅግ በጣም ትልቅ ማይኖሪቲ "አፋን ኦሮሞ ብቻ'' በሚል ፖሊሲ መገፋት አለበትን ?

3. "አድስ አበባ እንደ ሌሎቹ ትላልቅ የኦሮሚያ ዞኖች የዞን ደረጃ ተሰጥቷት፣ አማርኛ እና ኦሮምኛ የሥራ ቋንቋ ሆነው በኦሮሚያ ሥር እንድትተዳደር፣'' ሲሉ በአዲስ አበባ ዙሪያ ከዚህ በፊት ያልሰማሁት ሐሳብ አቅርበዋል። ከዚህ በፊት በሰጠሁት አስተያየት አዲስ አበባ በዙሪያዋ ያሉትን አካባቢዎች ያካተተ፣ አፋን ኦሮሞና አማርኛ የሥራ ቋንቋ የሆነበት፣ 10 ኛ ክልል ቢኖር ጥሩ የሚል ሐሳብ አቅርቤ ነበር። እኔ ያቀርብኩት ሐሳብ አቶ ብርሃነመስቀል ካቀረቡት ሐሳብ ጋር ይመሳሰላል። ልዩነቱ እርሳቸው አዲስ አበባ ብቻ ሲሆን ያሉት እኔ ደግሞ አዲስ አበባ እና አካባቢዋንም እጨምራለሁ። እርሳቸው ኦሮሚያ ዉስጥ ተኩኖ በዞን ደረጃ ይሁን ሲሉ እኔ ደግሞ ራሱን የቻለ ክልል ይሁን እላለሁ።

ሆኖም አቶ ብርሃኔ መስቀል ያቀረቡት ሐሳብ በጊዜያዊነት ተግባራዊ ቢሆን ችግር ይኖራል ብዬ አላስብም። እደግማለሁ እጊዜያዊነት። ይህእን ስል ግን ሁለት ነጥቦችን በማስቀመጥ ነው። አንደኛ አዲስ አበባን ለብቻ ዞን ከማድረግ ፣ የቡራዩ ልዩ ዞንና የሰሜን ሸዋ ዞንን ከአዲስ አበባ ጋር በማዋሃድ፣ አንድ ትልቅ ዞን በመፍጠር የዞኖኑ ቆዳ ስፋት ማስፋት ጥቅም አለው። ይህም ዞን በፌዴራል መንግስት ሥር የሚሆንን ሳይሆን፣ ተጠሪነቱ ለኦሮሚያ ክልል መንግስት ይሆናል። ሁለተኛ በሂደት ሕዝቡ ከፈለገ ዞኖችን ማዋሃድ፣ ወይንም ዞኖች የራሳቸው ክልል የመሆን መብት እንደሚኖራቸው ስምምነት መደረስ አለበት። አሁን ያለችው ኦሮሚያ የምትባለው ክልል በሕዝብ ፍላጎት የተመሰረተች ክልል አይደለችም። "ኦሮሚያ ወይም ሞት" የሚለው የአንዳንድ ኦሮሞ ብሄረተኞች አባባል ተቀባይነት የሚኖረው አባባል አይደለም። ሕዝቡ በፈለገ ጊዜ እንዴት መተዳደር እንዳለበት የመወሰን ሙሉ መብት አለው። ኦሮሚያን መቀየር አይደለም፤ ሕዝቡ ከፈለገ ፌዴራሊዝምን አልፈለግም ማለት ይችላል።

4. "በግፉ ለተገደሉና ለታሰሩ የኦሮሞ ልጆች ካሳ ተከፋሎ ገዳዮችና አሳርዎች ለፍርድ እንድቀርቡ'' በማለት ተጠያቂነትን እና ፍትህ መኖር እንዳለበት አቶ ብርሃነ መስቀል ይጽፋሉ። 200% እስማማለሁ።፡በትክክል መሆን ያለበት ነገር ነው።

5. " የኦሮሞ ሕዝብን ለ 140 ዓመታት ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የለየው ሥረዓት ተሽሮ ፣ ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ እንዲወጣ'' ሲሉ አቶ ብርሃነመስቀል በጻፉት ላይ ትንሽ ያልተመቸኝ ነገር አለ። ለ 140 አመታት ያሉት ምን ለማለት እንደፈለጉ ቢዘረዝሩት በስፋት ሐሳብ ለመስጠት ይረዳ ነበር። ይመስለኛል፤ በአይምሯቸው አጼ ሚኒሊክን እያሰቡ መሰለኝ።

አንደኛ እርሳቸው ምናልባት ወደሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ሄደው የሕዝቡን ሁቢመለከቱ ጥሩ ሊሆን ይችል ነበር። በይፋት፣ በመንዝ፣ በቆቦ፣. በአጽቢ፣ በአሳይታ ምን ያህል ሌላው ማህበረሰብ በድህነት የማቀቀ እንደሆኑ ይረዱ ነበር። ኦሮሞው ብቻ የኢኮኖሞ ተጠቃሚ እንዳልሆነ አድርገዉም አያቀርቡም ነበር። ሁለተኛ ታሪክን እያነሳን እንነጋገር ከተባለ ከመቶ አመት በፊት ሆነ የተባለውን ብቻ ሳይሆን ከሁለት፣ ሶስት፣ አራት መቶ አመታት በፊት በኢትዮጵያ ዉስጥ የተደረገዉን ልናነሳ እንችላለን። ይልቅ ተጣሞ የቀረበን ታሪክ እያነበበን ከመወነጃጀል፣ የወደፊቱን ላይ ብናተኩር የሚበጅ ይመስለኛል። ሂሳብ መተሳሰብ ከተጀመረ፣ ሌሎችም ሊመነዝሩት የሚችሉት ብዙ ነገር በእጃቸው እንዳለ እነ አቶ ብርሃነመስቀል መረዳት ያለባቸው ይመስለኛል።

6. “የኦሮሞ ሕዝብ በክልል ደረጃ ከፌዴራል ተላላኪዎ እጅ ወጥቶ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድርና በፌዴራል ደረጃ ኢትዮጵያን በድርሻው ልክ ተወክሎ እንዲያስተዳድር” ሲሉ አቶ ብርሃነመስቀል ስድስተኛ ነጥባቸዉን ያስቀምጣሉ። የፌዴራል ስርዓት እስከሆነ ድረስ ያለው በአገሪቷ የፌዴራል ስርዐት የተቀመጡ ሕጎች መከበር አለባቸው። ሕግ የበላይ ካልሆነ የፌዴራል ስርዓት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። አምባገነናዊ ስርዓት ብለበት ሁኔት ፌዴርሊዝም አይሰራም።፡በመሆኑም እዉነተኛ ፌዴራሊዝም እንዲኖር ሕግ የበላይ የሆነበት ስርዓት መኖር አለበት። የፌዴራል መንግስት ከሕግ ውጭ በክልል ዉስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም። ክልሎችም በዞን እና በወረዳ አስተዳደሮች ሕጉ ከሚፈቅድላቸው ዉጭ ጣልቃ መግባት የለባቸው። ላችንንም ሕግ ከገዛን ነገሮች ይስተካከላሉ።

ተዛማጅ ፅሁፎች:

የኦሮሚያ ክልል አስተዳደር «ኦሮሞዉን» ጎድቷል
ጃዋር ነበር የሚለው፣ አሁን ግን የኦሮሞ ተማሪዎችም ደገሙት – ኦሮሚያ የኦሮሞዎች ናት (ናኦሚን በጋሻዉ)
የአባይ ጸሃዬ ጦርነት በሚለው ላይ ምላሽ ለተስፋዬ ገብረአብ – ግርማ ካሳ
ቋንቋ መግባቢያ ነው ፤ ከዚያ ዉጭ ማየት ዘረኝነት ነው – ግርማ ካሳ